በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ ጋብቻ - ክፍል 3


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon3@gmail.com


*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

## ሚያዝያ ፲፫ ቀን ፳፻፲ ዓ.ም.

# የሕይወት አጋር ምርጫ

- ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በተወለደው በጌታችን በኀጢአት የጎሰቆለው የቀድሞ ሕይወታችን ታድሶ ተለውጧል፡፡ በበደልንም ጊዜ በንስሐ ታጥበን መልሰን እንነጻለን፡፡
- ሰው ሁሉ በዚህ ዓለም የሚፈጽመው ተልዕኮና ይህንንም የሚያከናውንበት የሕይወት አቅጣጫ አለው፡፡
- ***ተልዕኮአችን ምንድር ነው?*** ዘላለማዊ ሕይወት ነው፡፡ አቅማችን በፈቀደው መጠን ሁሉ ሰዎችን ወደ ዘላለማዊ ሕይወት ማቅረብ ወደ አባታችንም ወደ እግዚአብሔር እቅፍ ማስገባት ነው፡፡
- ተልዕኮአችን የሚገጥሙንን ፈተናዎች ሁሉ ተቋቁመን በአምላካችን ጥበቃ ወደ ዘላለማዊት ሕይወት መድረስና ሌሎችንም ማድረስ ነው፡፡
- ***የሕይወት አቅጣጫችን ወይም ፍልስፍናችንም*** እንደ ክርስቶስ ሆኖ መኖር ነው፡፡
- ***ሚናችን*** ደግሞ እንደ ማንነታችን ይለያያል፡፡ ሚናችን አባት፣ እናት፣… መሆን ነው፡፡ በየሚናችንም የምናከናውነው የተለያየ ድርሻ አለን፡፡
- እንደ አባት ሚስትን መውደድ፣ ልጆችን በፈሪሃ እግዚአብሔር ማሳደግ፣ ወዘተ ደግሞ ይኖራል፡፡ ይህም ግብ ነው፡፡ ***ግብ*** ከሕይወት አቅጣጫ (ፍልስፍናና) ከተልዕኮ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚጓዙ ናቸው፡፡
- የአንዳንዱ ተልዕኮ ባለጠጋ መሆን፣ ተምሮ ብዙ ዲግሪዎችን መያዝ ይሆናል፡፡ ተልዕኮ ግን የሕይወት ፍልስፍናንና ግብን ይፈልጋል፡፡

# ጋብቻና ምንኩስና

- ሁለቱም የሕይወት መንገዶች የየራሳቸው ፈተና ያላቸው ሲሆኑ ጋብቻ ግን የተሻለ ምርጫ ነው፡፡
- በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኒቂያ ጉባኤ በተደረገ ጊዜ ሕጋውያን (በትዳር የሚኖሩ) ቀሳውስትን ቀድሰው እንዳያቆርቡ ወደ ቤተመቅደስም እንዳይገቡ የሚያደርግ እንቅስቃሴ ነበር፡፡
- ይሁን እንጂ በዚህ ጉባኤ ይህንኑ በጥልቀት በመመርመር ጋብቻ ታላቅ ምስጢር መሆኑንም በመረዳት በጋብቻ ነውር ሳይሆን ክብር እንደሆነ በማመን ለተፈጠሩት እንቅፋቶች መፍትሔ በማስቀመጥ ***ቅስና*** ያገቡ ዲያቆናትም ሆኑ የማያገቡ መነኮሳትም የሚያገለግሉበት ሹመት እንደሆነ ወስነዋል፡፡
- በካቶሊኮች ዘንድ ለካህናቶቻቸው በአጠቃላይ ማግባት አይፈቀድም፡፡
- ለእናንተ የሚሻለው ጋብቻ ወይስ ምንኩስና?
- ለእኔ የቱ ይሻለኛል? ጋብቻ ወይስ ምንኩስና? በማለት የምንመርጥ ከሆንን በዚህ አካሄድ የምንገባው ለጋብቻ እንደሆነ እንረዳ፡፡ ምክንያቱም ለምንኩስና የሚገቡት ይኽን አሳብ ፈጽመው አያስቡም ትኩረትም አይሰጡትምና፡፡
- መነኮሳት ጋብቻ ታላቅ ምስጢር ቢሆንም ለእኛ ግን አይደለም ብለው ምንኩስናን በመምረጥ ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ሙሽራ ይሆናሉ፡፡
- መነኩሴ ለመሆን ከፈለግን ወደ ገዳም ከመሄዳችን አስቀድሞ በምንኩስና ሕይወት ለመኖር ከቤታችን ጀምሮ ዝግጅት እናድርግ፡፡

# ጋብቻና ምንኩስና

- ጋብቻም ምንኩስናም ሁለቱም የተመረጡ ሚናዎች ቢሆኑም ምንኩስና ግን ለተመረጡት እንጂ ለማንም እንደማይሆን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ "በእናት ማኅፀን ጃንደረቦች ሆነው የተወለዱ አሉ፥ ሰውም የሰለባቸው ጃንደረቦች አሉ፥ ስለ መንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ፡፡ ሊቀበለው የሚችል ይቀበለው አላቸው፡፡" *ማቴ 19፡12፡፡*
- ለሰው የተዘጋጀለት ምንድር ነው? ጋብቻ ነው፡፡
- በምንኩስና ተለይተን ለመኖር ከመረጥን አስቀድሞ የንስሐ አባታችን በአግባብ ሊያውቁን ይገባል፡፡
- የንስሐ አባታችን ፈቅደን ልባችን የተሰበረ መሆን አለመሆኑን መመርመርና ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ልብ ካልተሰበረ ይኸም በመንፈሳውያኑ አባቶች አስቀድሞ ካልተመረመረና ካልታወቀ ሕይወቱ ምንኩስና ሊሆን አይችልም፡፡
- ጳጳስ እሆናለሁ ብሎ በማሰብ የተከፈለ ልብ ይዞ መነኩሴ አይኮንም፡፡ የቀሰቀሰን ምክንያት የተሳሳተ ነው፡፡
- ለምንኩስና ሕይወት የሚያነሳሳን በላያችን በተዘጋው ባዕታችን ውስጥ ከሙሽራው ከጌታችን ከመድኃኔዓለም ጋር ለመሞትና ለመኖር መወሰን ነው፡፡
- በምንኩስና ሕይወት ወደ ሙሽራው ወደ ጌታችን በሞት እስክንወሰድ ድረስ ገዳምን ትቶ መውጣት አይኖርም፡፡ ምንኩስና ማለት በጥቂቱ ይኸው ነው፡፡

# ለጋብቻ የሚያነሳሳን ምክንያት ምንድር ነው?

- ለጋብቻ የሚያነሳሱ ትክክለኛ ምክንያቶች አሉ፡፡ ከእነዚህም አንድ ሆኖ መረዳዳት፣ ዘር መተካትና ከፍትወት መጠበቅ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

*ለጋብቻ የሚያነሳሱ ትክክለኛ ምክንያቶች*

- አንድ ሆኖ መረዳዳት፡፡ (1+1=1) "እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው፦ ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው፡፡" *ዘፍጥ 1፡28፡፡*
- ዘር መተካት፡- ልጅ ቢኖረንም ባይኖረንም አንድነቱ ይቀጥላል፡፡ ልጅ ባይኖረን ወላጅ የሌላቸው ሁሉ ልጆቻችን ይሆናሉ፡፡ ልጆች መውለድ መንከባከብ ማታላችንንም መመርመር ይፈልጋል፡፡
- ከፍትወት መጠበቅ (ንጽሕና)፡- "ነገር ግን በምኞት ከመቃጠል መጋባት ይሻላልና ራሳቸውን መግዛት ባይችሉ ያግቡ፡፡" ቀዳ ቆሮ 7፡9፡፡ "ዳሩ ግን ማግባት ወደሚገባው ዕድሜ በደረሰ ጊዜ ስለ ድንግልናው ያፈረ ሰው ቢኖር፥ የወደደውን ያድርግ፤ ኃጢአት የለበትም፤ ይጋቡ፡፡" ቀዳ ቆሮ 7፡36፡፡

*ለጋብቻ የሚያነሳሱ የተሳሳቱ ምክንያቶች*

- *ፈቃደ ሥጋን መፈጸም*

# <u>የሕይወት አጋራችንን እንዴት እንመርጣለን?</u>

- መምረጥ 12 ሴቶችን ደርድሮ መምረጥ ነው???
- eHarmony የሚባል ዌብ ሳይት አለ፡፡ ማንነታችሁን ከፎቶግራፍ ጋር ልካችሁ እነርሱ ለናንተ የሚሆነውን መርጠው ይልካሉ፡፡ አንዳንዶች ቢንቁትም ማንነታቸውን ደብቀው ስምም ለውጠው የሚሞክሩ አሉ፡፡ www.heart-of-asia.com ለዚህ ጥሩ ተጠቃሽ ብዙዎች የሕይወት አጋር እናገናለን የሚሉበት የሞኝነት አዳራሽ ነው፡፡
- ታዲያ የሕይወት አጋር አድርጌ የመረጥኩት የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑን በምን አውቃለሁ?
- ያገባችሁ በምትማሩት ያለፉትን የሁለት ሳምንታት ትምህርት ጨምሮ ራሳችሁን መርምራችሁ አስተካክሉበት፡፡

<u>የሕይወት አጋራችንን የምንመርጥባቸው አራት ቁልፍ መንገዶችና አሥር መመዘኛዎች አሉ፡፡</u>

1. *<u>የንስሐ አባት፡-</u>* ወደ ምናደርገው የሕይወት አጋር ምርጫ፣ ወደመተጫጨት ብሎም ወደጋብቻ የሚመሩን የንስሐ አባት መኖር፡፡ የንስሐ አባት መኖሩ የግድ አስፈላጊ ነው ይመራናልና፡፡ ከአባታችንም ጸሎታቸው፣ ትምህርታቸውንና የሚመሩንን አቅጣጫ ሁሉ የምንጠቀምበት መሆን ይገባናል፡፡
    - ለንስሐ አባታችን ከነገርን ነገሩ እርግጠኛ መሆን አለመሆኑን በጥልቀት መርምረው ወደ አንድ አቅጣጫ ይመሩናል፡፡

# የሕይወት አጋራችንን እንዴት እንመርጣለን?

**የሕይወት አጋራችንን የምንመርጥባቸው አራት ቁልፍ መንገዶችና አሥር መመዘኛዎች አሉ።**

2. ጸሎት፣ ጾምና ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ፡-
   - ተረጋግተን ጸሎት በማድረግ፣ በመጾምና ቅዱሳት መጻሕፍት የሚሉንን በማንበብ ተረጋግተን ከተጓዝን ነገንም በእርጋታ መሻገር እንችላለን።
3. የወላጆቻችን ምርቃት
   - ያለ ወላጆቻችን ምርቃት ትዳር ለመመሥረት መጣደፍ የለብንም።
   - ከእግዚአብሔር የሆኑ ወላጆቻችን ነነልተቀበሉት ከሆነ በጋብቻው ችግር ይገጥመናል።
   - የንስሐ አባቶቻችን ነነህን አስመልክቶ በእጅጉ ሊረዱን ይችላሉ።
   - ስለዚህ የወላጆቻችንን ምርቃት እስክናገኝ ድረስ ያለንን ዕቅድ ሁሉ ማራዘም ይኖርብናል።
   - መሆን የሚገባውን ይህን ጉዳይ ንቀን ብናልፈውና ነገ ወላጆቻችን በጋራ በአንድ ላይ በአንድ መርሐ ግብር ሲገኙ ምን እናደርጋለን? ለምሳሌ የአንዱ ወገን ወላጅ በሃይማኖቱ የጠነከረ ቢሆን ሌላኛው ደግሞ ምንም ባይረዳ ሲገናኙ የሚጨዋወቱት ስለምን ይሆን?...
4. መልካም አጋጣሚዎች
   - ዕቅዳችን ዕንቅፋት ሲሰሰልፍ ሌላ ዕንቅፋት፣ አንዱን የተዘጋ ደጅ ስናልፍ ሌላ የተዘጋ በር ደጋግሞ የሚገጥመን ከሆነ ውሳኔያችንን መመርመር ይገባናል።
   - ነገር ሁሉ መልካም ከሆነም ከእግዚአብሔር እንደሆነ እንረዳ።

# <u>የሕይወት አጋራችንን የምንመርጥባቸው አሥሩ መመዘኛዎች?</u>

<u>**እነዚህ መመዘኛዎች ለውሳኔ ይረዳን ዘንድ የተሰጣቸው ፐርሰንት አለ፡፡ ፐርሰንቱም 100% መመሆናል፡፡**</u>

- ከ75 — 100% ካገኘን ስጦታው ከእግዚአብሔር እንደሆነ እናውቅበታለን፡፡ ከ90% በላይ ግን የሚያገኝ አይኖርም

1. መንፈሳዊ ሕይወት (አምላካችን ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ ሕይወት)
    - በየዕለቱ ቤተ ክርስቲያን መምጣታችንን፣ አገልጋዮች መሆናችንን፣ ዘወትር መጸለያችንን፣ በየሳምንቱ መቁረባችንን፣ … ማለት ኤአደለም፡፡ ከዚያ ያለፈ ነው፡፡
    - አመለካከታችን፣ አስተሳሰባችን፣ ከአንደበታችን የሚወጡ ቃላቶች፣ ጠባያችን፣ ስሜታችን … ወዘተ አምላካችን ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ እርሱን የሚያስመስለን ነው?
    - በየዕለቱ ቤተ ክርስቲያን መምጣታችንን፣ አገልጋዮች መሆናችንን፣ ዘወትር መጸለያችንን፣ በየሳምንቱ መቁረባችንን፣ … ብቻ በቂ ኤአደለም፡፡
    - አመለካከታችን፣ አስተሳሰባችን፣ ከአንደበታችን የሚወጡ ቃላቶች፣ ጠባያችን፣ ስሜታችን … ወዘተ የተቀደሰ ካልሆነ አምላካችን ክርስቶስን ማዕከል ያደረግን እርሱንም የምንመስል አይደለንም፡፡
    - እውነተና አገልጋይ በቤት ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስት ሳይሆን ትክክለኛና ግልጥ በሆነው በራሱ ማንነት ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡
    - በቤተ ክርስቲያን እየተገኙ መጠጥ የሚያቀርቡ፣ ዕፅ የሚመመዘዋውሩ፣… የሚጠነቁሉ የሚያስጠነቁሉ ይኖራሉና መጠንቀቅ ይኖርብናል፡፡

# የሕይወት አጋራችንን የምንመርጥባቸው አሥሩ መመዘኛዎች?

- ልቅ የሆኑ የወሲብ ፊልሞችን የተለማመዱ ብዙዎች ይኖራሉና መጠንቀቅ ይገባል፡፡
- አምላካችን ክርስቶስን ማዕከል ማድረግ እርሱንም መምሰል በነፍሳችን በመንፈሳችንና በሥጋችን የርሱን ምሳሌነት መከተል ነው፡፡
- ነገሮችን ሁሉ በርጋታ ተቀምጠን እንመርምር፡፡
- ይሕ መመዘኛ ብቻውን 50% ይይዛል፡፡
- ከ2 — 10 ያሉት መመዘኛዎች ቅደም ተከተል የላቸውም፡፡ እንደ ፍላጎታችሁ ቅደም ተከተል ስጡት፡፡ በአጠቃላይም 45% መመህሉን ድርሻ ይይዛሉ፡፡

2. ቤተሰብ

- የርሷና የኔ ቤተሰብ ተቀላቅሏል? አንዱ ሌላውን መገንዘብ ይችላል?
- በአንዳንድ ማኅበራዊ አጋጣሚዎች በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ተነጋግረው መግባባት ይችላሉ? በአስተሳሰብም ሆነ በአመለካከት መቀዳደም የለም? ስለ ቤ/ክ፣ ስለ ቅዱሳን የሚነጋገሩት ያግባባቸዋል?
- ከቀለበት በፊት የሌላውን ወላጅ ለመጎብኘት እንሄዳለን? አዎ ሁለቱ ሦስቴ ቢበበንስ መሄድ ይጠበቅብናል፡፡
- በአንዳንድ ጉዳዮች ባለመግባባት አንዱ ዝም ብሎ ተናጋሪ አንዱ አዳማጭ እየሆነ መመጣጠን የሚጠፋባቸው በርካታ አጋጣሚዎች አሉ፡፡

# የሕይወት አጋራችንን የምንመርጥባቸው አሥሩ መመዘኛዎች?

3. ከሰው የመግባባት ችሎታ
   - ማዳመጥ፣ መረዳት፣ ራስን መግለጥ፣ ...
   - አብረን ስንቀመጥ መግባባት እንችላለን?
   - አንተ/እርስዋ ንግግራችሁ ያበሳጫችኋል?
   - እርስዋ ስለ ኢኮኖሚክስ የመመረቂያ ጥናትዋ ወይም ምርምርዋ ልታስረዳ ልትናገር ትችላለች። ነገር ግን ይኸ ያግባባናል? መደማመጥ እንችላለን?
   - በዚህ ሂደት አንዱ ሌላውን የመመዘን ዕድል ያለው ሲሆን የመግባባት ችሎታችንንም ደረጃ ይገልጣል።
4. ስሜትን መግለጽ
   - ስሜትን መቆጣጠር መቻል።
   - የተዘበራረቀ ስሜትን፣ ንዴትን፣ ብስጭትን፣ ሁከትን፣ ርኅራኄን፣ መነካታችንን የምንገልጽባቸው መንገዶች ብስለት
5. በማኅበራዊ ሕይወት ያለን ብቃት
   - ከሰው ጋር መቀራረብ፣ ጓደኞቻችን ጋር ያለን መቀራረብና መራራቅ፣ ...
   - ጋብቻን ለመመሥረት ካሰብን ራሳችንን መቆጣጠር ባልቻልንባቸው ምክንያቶች፣ አደንዛዥ ዕፅ በመጠቀምና ባለመጠቀም፣ ቁማርን፣ ያልተገደበ ወጪያችንን፣ ወዘተ በተመለከተ ያለንን ብቃት እንገምግም።

# የሕይወት አጋራችንን የምንመርጥባቸው አሥሩ መመዘኛዎች?

6. ኃላፊነት የሚሰማን መሆንና ቅንነት
   - ልጆችን፣ ቃላችንን፣ ጠባያችንን በተመለከተ እምነት የሚጣልብን ነን?
   - የንስሐ አባታችን እርሱ እምነት የሚጣልበትና ቅን ሰው ወይም እርሷ እምነት የሚጣልባት ቅን ሰው ስለመሆኗ ሙሉ በሙሉ ምስክርነት ልሰጥ እችላለሁ ይሉልናል?
   - ውስጣዊ ብስለታችን ምን ያህል ነው?
7. የሥራችንና የምናገኘው ገቢ ሁኔታ የተረጋጋ መሆን
   - ፍቅር ብቻ ሳይሆን በዚህ ዓለም ለመኖር የምንሠራው ሥራ፣ ሠርተን የምናገኘው ገቢ ያስፈልገናል፡፡
   - ወደ ጋብቻ ሕይወት ለመግባት የራሳችን ሞያ ወይም ዕውቀት ያለን መሆን አስፈላጊ ነው፡፡
8. ተክለ ቁመናና መልክ
   - ምን ያህል ቆንጆ ወይም ውብ፣ ረጅም ወይም አጭር፣ ጥቁር ጠይም ወይም ቀይ፣ ወፍራም ወይም ቀጭን መሆንን መምረጥ

   ማስጠንቀቂያ

   - በዚህ መመዘኛ ብቻ ከ90-100% ሰጥታችሁ ያገኙ ካሉ ባታገቡ የተሻለ ነው፡፡ ምክንያቱም በፍትወት ብቻ መሳባችንን የሚያሳይ ስለሆነ ነው፡፡ ዳሌ፣ ቀለም፣ ወገብ የምንመርጥ ከሆንን እንጠንቀቅ፡፡

# የሕይወት አጋራችንን የምንመርጥባቸው አሥሩ መመዘኛዎች?

- ይህን የፈለግነውን ዓይነት ውበት የተለያዩ ኮስሞቲኮችን ወይም ፕላስቲክ ሰርጀሪ በማድረግም ቢሆን ማምጣት ይቻላል፡፡… ቀድመን ያላወቅነውን ሰው ሠራሽ ጥርስ አውልቆ መተኛትን ከጋብቻ በኋላ ስናውቅ መደንገጥ እንዳይኖር ይኽን መመዘኛ ከሌላው የበለጠ ላለማድረግ እንጠንቀቅ፡፡
- ብዙ ሺ ብር በማውጣት ለመንፈሳዊ ሕይወት ግን ፕላስቲክ ሠርጀሪ ማድረግ አይቻልም፡፡
- ስለዚህ ዓይናችንን ከድነን ለሕይወት አጋርነት በመረጥነው/በመረጥናት ውስጥ ምን እንዳለ በጥልቀት እንመልከት፡፡
- በውጪው ውበት ላይ እጅግ አትኩሮት የምናደርግ ከሆንን አእምሮአችን መቆሸሹን እንወቅ፡፡
- የአፍንጫዋ ቀዳዳ አንዱ ከአንዱ ይበልጣል አንዱ ሰፋ ይላል ብለው ሌላውን ጥሩ ገጽታ ንቀው በምርጫቸው የሚሳሳቱ አሉ፡፡
- ዛሬ አንዳንዶች የተዘፈቁበት ልቅ የሆነ የወሲብ ፊልም የትዳር ገዳይ ነው፡፡ ይህም የቅድስና መታጣት ምልክት ነው፡፡

9. ጤንነት

- ስኳር፣ ጉበት፣ ካንሰር፣… ወዘተ ካለ ሳይደበቅ መቀለጥ መቻል አለበት፡፡
- አንዳንድ ጊዜ ሳቀቀነገር ቀርቶ የተደበቀ በሽታ ትዳሩን ይጎዳልና አስቀድሞ ታውቆ ተነጋግሮ መፍትሔ እንዲደረግለት ይገባል፡፡

# የሕይወት አጋራችንን የምንመርጥባቸው አሥሩ መመዘኛዎች?

10. አእምሮአዊ ጤንነት

    - የአእምሮ ጭንቀት፣ እብደት... ወዘተ ያለ መሆን አለመሆኑን ቃል ኪዳን ከመግባታችን፣ ፊርማችንን ከማኖራችንና፣ ከመፈራረማችን በፊት ማረጋገጥ - ከተጋቡ በኋላ መፋታት የለምና።

- ሌሎች ያልተጠቀሱ መታየት ያለባቸው ጉዳዮች ሳይጋነኑ ሊታከሉ ይችላሉ።

- ከ2 — 10 ያሉትን ለእያንዳንዳቸው 5% እየሰጠን ብንደምራቸው 45% ይሆናሉ።

- እኛ በራሳችን ገምግመን የተዋጣልን ስለማንሆን የተረፈውን 5% ለራሳችን እንስጥ።

- ከዚህ በላይ ያሉትን መመዘኛዎቻችንን ይዘን በሕይወታችን ሁሉን ወደ ሚመሩ ሁሉን ወደሚወስኑ የንስሐ አባቶቻችን ይዘን በመሄድ በመጨረሻ ውሳኔያችን የተጣራ ውጤት ያለን እንሁን።

- እግዚአብሔር የሕይወት አጋርን በወላጆቻችን፣ በጓደኞቻችን ... አቅራቢነት ወይም አማካይነት ሊሰጠን ይችላልና የምንንቀው የእግዚአብሔር ሥራ አይኑር።

- ከዚህ ባለፈ መመዘኛችንንም ሆነ ተመዛጮችን አናብዛ... እንዳንቸገር።

... ክፍል አራት ይቀጥላል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።